የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ–ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 4
ADDIS ABABA–24th October, 2002


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
ከዴንማርክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፱፻፴፫


## CONTENTS


Proclamation No. 292/2002
Promotion and Reciprocal Protection of Investment Agreement with the Kingdom of Denmark Ratification Proclamation. ......................Page 1933


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዴንማርክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በዴንማርክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ሚያዚያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም· በአዲስ አበባ የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገር ህጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ ከ፴ ቀናት በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለፀ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ «ከዴንማርክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፪/፲፱፻፺፭» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO. 292/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION OF INVESTMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KINGDOM OF DENMARK*

*WHEREAS,* the Agreement on Promotion and Reciprocal Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of Denmark is signed in Addis Ababa on the 24th day of April, 2001;

*WHEREAS,* it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force 30 days after the last date on which the contracting parties have notified each other that the Constitutional requirements for the entry into force of the Agreement have been fulilled;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 24th day of October, 2002;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Promotion and Reciprocal Protection of Investment Agreement with the Kingdom of Denmark Ratification Proclamation No. 292/2002."


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዴንማርክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

፫. <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ኃላፊነት</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment signed, in Addis Ababa on the 24th day of April, 2001, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Denmark is ratified.

3. *Power of the Ethiopian Investement Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of October, 2002.

Done at Addis Ababa, this 24th day of October, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE